የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 49
ADDIS ABABA–17th April 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፱/፲፱፻፺፭ ዓ·ም

የንግድ አሠራር አዋጅ ............................... ገጽ ፪ሺ፩፻፶፪

CONTENTS

Proclamation No. 329/2003

Trade Practice Proclamation .................. Page 2152

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፱/፲፱፻፺፭
## የንግድ አሠራር አዋጅ

የንግድ ሥራ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት ተገቢውን አሠራር ተከትሎ መካሄድ ስላለበት፣

ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋነትንና ማኅበራዊ ደኅንነትን ለማስፈን እና በነጋዴዎችም መካከል የሚደረጉትን ፀረ–ውድድር የሆኑ ተግባራት በመቆጣጠር ለውድድር አመቺነት ያለው ሥርዓት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መሠረታዊ በሆኑ አንዳንድ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ዋጋን መቆጣጠርና ሥርጭቱንም ሥርዓት ማስያዙ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የንግድ አሠራር አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፱/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩· "መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት" ማለት በገበያ ላይ ዕጥረት በመፈጠሩ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ ሊያስከትል የሚችል ከሸማቹ የዕለት ቁሳዊ ፍላጎት ጋር የተገናኘ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው።

## PROCLAMATION No. 329/2003
## TRADE PRACTICE PROCLAMATION

WHEREAS, it is necessary, that trade practice must be undertaken in accordance with the free-market economic policy of the country;

WHEREAS, it is desirable to establish a system that is conducive for the promotion of competitive environment, by regulating anti-competitive practices in order to maximize economic efficiency and social welfare.

WHEREAS, it is believed that the regulation of price and equitable distribution of certain basic goods and services in times of irregular and short supply is necessary to safeguard the public;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*

This Proclmation may be cited as "Trade Practice Proclamation No. 329/2003."

2. *Definitions*

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1) "Basic goods or services" means goods or services related to the daily material need of the consumer, the shortage of which in the market may lead to unfair trade practice;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3·40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የንግድና ኢን ዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፫· "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት የንግድና እንዱ ስትሪ ሚኒስቴር ወይም ክልል የሚመለከተው ቢሮ ነው፡፡

፬· "ተጠቃሚ" ማለት ለራሱ ፍጆታ ከነጋዴ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚገዛ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

፭· "ኮሚሽን" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋም አካል ነው፡፡

፮· "የንግድ ዕቃ" ማለት ለገንዘብነት ከሚውል ከወርቅ ገንዘብ፣ ከማንኛውም ዓይነት ገንዘብ፣ ከሌላ መገበያያ ገንዘብ፣ ገንዘብነት ካላቸው ሰነዶችና ከግል መገልገያዎች በስተቀር የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎች ማለት ነው፡፡

፯· "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፰· "አገልግሎት" ማለት ደመወዝ ወይም የቀን ሙያተኛ ክፍያ ያልሆነ ገቢ የሚያስገኝ ማናቸውም አገልግሎት የመስጠት ንግድ ሥራ ነው፡፡

፱· "ጽሕፈት ቤት" ማለት በሚኒስቴሩ መዋቅር ሥር ያለና ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ኃላፊነት የሚሰጠው መምሪያ ነው፡፡

፲· "ነጋዴ" ማለት የሙያ ሥራው አድርጎ ጥቅም ለማግኘት ሲል በንግድ ሕግ ቁጥር ፭ የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ወይም መንግሥት የንግድ ሥራ ነው ብሎ በሕግ የሚወስነውን ሥራ የሚሠራ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

፲፩· "የንግድ ሥራ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) በተተረጎመው መሠረት ነጋዴ የሚሠራው ሥራ ነው፡፡

፫· ዓላማ

፩· ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ለማድረግ፣ እና

፪· በንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት እና ሥርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጊቶችን በመከላከልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡

፬· የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በማንኛውም በንግድ ሥራ ላይ በተሠማራ ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭· ልዩ ሁኔታዎች

የዚህ አዋጅ አንዳንድ ድንጋጌዎች ቀጥሎ በተመለከቱት ላይ ተፈጻሚ ስለማይሆኑበት ሁኔታ በኮሚሽኑ ሊወሰን ይችላል፡፡

፩· በኢንቨስትመንት አዋጁ መሠረት በመንግሥት ብቻ በሚካሄዱ የንግድ ሥራዎች፣

፪· በመንግሥት ትኩረት ሊሰጣቸውና ዕድገታቸው እንዲፋ ጠን ለታቀዱ ለልማት ጉልህ አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ ድርጅቶች፣ እና

፫· የዋጋ ቁጥጥር በሚደረግባቸው መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፡፡

ክፍል ሁለት
ፀረ ውድድር ስለሆኑ ተግባራት

፮· ክልከላ

፩· ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማምረት፣ በአቅርቦት፣ በስርጭት ወይም ዕቃና አገልግ ሎትን በመገበያየት ሂደት ውስጥ የነፃ ገበያ ውድድርን የሚገድብ፣ የሚቀንስ፣ የሚከለክል ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ የሚጎዳ የጽሑፍ ወይም የቃል ስምምነት ማድረግ አይችልም፡፡

2) "Ministry" or 'Minister" means the Ministry or Minister of Trade and Industry respectively;

3) "Appropriate Authority" means the Ministry of Trade and Industry or the concerned Regional Bureau;

4) "Commission" means a body established by this Proclamation at a Federal level;

5) "Consumer" means any person who buys goods or services for personal consumption;

6) "goods" means movable commodities, except monetary gold, moneys in any form, other means of payment, securities and personal effects;

7) "Person" means any physical or juridical person;

8) "Service" means any dispensing of service for consideration other than salary or wages;

9) "Secretariat" means a department under the organizational structure of the Ministry, to undertake the responsibility of executing this Proclamation.

10) "Trader" means any person who professionally and for gain carries on any of those activities specified under Article 5 of the Commercial Code, or who dispenses services, or who carries on those commercial activities designated as such by laws issued by the Government.

11) "Commercial Activity" means any activity carried on by a business person as defined under Sub-Article (10) of this Article.

3. *Objective*

1) To secure fair competitive process through the prevention and elimination of anti-competitive and unfair trade practices, and

2) To safeguard the interests of consumers through the prevention and elimination of any restraints on the efficient supply and distribution of goods and services.

4. *Scope of Application*

This Proclamation shall apply to all person involved in any commercial activity.

5. *Exceptions*

Non-applicability of certain provisions of this Proclamation on the following cases may be decided by the Commission.

1) Commercial activities that are, according to investment proclamation, exclusively reserved for the Government.

2) Enterprises having significant impact on development and designed by the Government to fasten growth and facilitate development.

3) Basic goods or services that are subject to price regulations.

PART TWO
*Anti-Competitive Practices*

6. *Prohibition*

1) No person may directly or idirectly enter into any written or oral agreement that restricts, limits, impedes or in any other way harms free competition, in the process of production, supply, distribution or marketing of goods and services.

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋር እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድርጊቶች ፀረ ውድድር ስምምነቶች እንደሆኑ ይቆጠራሉ፣

ሀ) ዋጋን በጋራ የመወሰን ስምምነት፣

ለ) የገበያ ዋጋን ለመወሰን በሽርክና ለመጫረት የሚደረግ ስምምነት፣

ሐ) ገበያን ወይም ደንበኞችን መመደብ የመከፋፈል ስምምነት፣

መ) የምርትና ሽያጭ ኮታ ምደባ ስምምነት፣

ሠ) ላለመሸጥ፣ አገልግሎት ላለመስጠትና ላለመደ ራደር በሕብረት አቋም መያዝ።

፯· <u>ስለመፍቀድ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ስምምነቱ ከሚያደርሰው ጉዳት የላቀ ለአገሪቷ የሚሰጠው ጥቅም የሚያመዝን መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢውን ግዴታ አስገብቶ ስምምነቱ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።

፰· <u>ምዝገባ</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ መሠረት የተፈቀደና በጽሑፍ የተደረገው ስምምነት ዝርዝር ጉዳይ በሚኒስቴሩ ውስጥ በሚገኝ ልዩ መዝገብ እንዲገባ ሆኖ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል።

፱· <u>ምዝገባን ስለመሰረዝ</u>

ስምምነቱ ከተፈጸመ በኋላ ለሀገሪቷ ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ከሆነ ወይም ተስማሚ ወገኖች በገቡት ግዴታ መሠረት ካልፈጸሙ ሚኒስቴሩ የሰጠውን ፈቃድ ሊሠረዝ ይችላል።

፲· <u>ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር</u>

፩· በንግድ ሥራ ሂደት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ተወዳዳሪን ለማጥፋት ያለመ ማንኛውም ድርጊት ወይም ተግባር ሁሉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር እንደሆነ ይቆጠራል።

፪· በተለይም የሚከተሉት ድርጊቶች ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ውድድሮች እንደሆኑ ይቆጠራሉ፡

ሀ) በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች፣ በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊት፣

ለ) በሌላው ድርጅት መልካም ስም ወይም ዝና ላይ ሀሰት በሆነ አፈጻጸም ጉዳት ያደረሰ ወይም ሊያደርስ የሚችል ማናቸውም ድርጊት፣

ሐ) የአንድን ድርጅት ወይም የድርጅቱን ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብን ግንዛቤ ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል ማናቸውም ድርጊት፣

መ) ባለመብት ከሆነው የመረጃው ባለቤት ፈቃድ ውጭ ከሐቀኛ የንግድ አሠራር ተፃራሪ በሆነ ሁኔታ የሌላውን መረጃ የማውጣት የመያዝ ወይም የመቀጠም ማናቸውም ድርጊት፣

ሠ) የሌላውን የንግድ ድርጅት ወይም የድርጅቱን ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ታማኝነትን ያሳጣ ወይም ሊያሳጣ የሚችል ማናቸውም ሀሰት የሆነ ወይም ማረጋገጫ የሌለው አገላለጽ፣

2) Without prejudice to the generality of sub-Article (1) of this Article, the following agreements shall be deemed to have been anti-competitive;

(a) Agreements of jointly fixing prices;

(b) Agreements for collusive tendering as to determine market price;

(c) Agreements as to market or consumer segmentation;

(d) Agreements as to allocation by quota of production and sales;

e) Concerted refusal to deal, sell and render services.

7. *Authorization*

Notwithstanding the provision of Article 6(1) of this Proclamation, the Ministry may authorize entry into any such agreement, subject to undertaking of appropriate commitments, after making the necessary studies, and ensuring that advantages of the agreement to the Nation is greater than the disadvantages.

8. *Registration*

Particulars of an authorized agreement done in writing, pursuant to Article 7 of this Proclamation, shall enter in a special register, at the Ministry and be open to the public.

9. *Cancellation*

The Ministry may cancel authorization of any agreement in the event that the advantages to the Nation are no longer greater than the disadvantages or the parties agreed fail to comply with the terms and conditions of the Agreement.

10. *Unfair Competition*

1) Any act or practice, in the course of commercial activities, that aims at eliminating competitors through different methods shall be deemed to be an act of unfair competition.

2) The following activities, in particular, shall be deemed to be acts of unfair competition.

(a) Any act that causes, or is likely to cause, confusion with respect to another enterprise or its activities, in particular, the products or services offered by such enterprise;

(b) Any act that damages, or is likely to damage the goodwill or reputation of another enterprise falsely;

(c) Any act that misleads or is likely to mislead the public with respect to an enterprise or its activities, in particular, the products or services offered by such enterprise;

(d) Any act of disclosure, acquisition or use of information without the consent of the rightful holder of that information in a manner contrary to honest commercial practice;

(e) Any false or unjustifiable allegation that discredits, or is likely to descredit with respect to another enterprise or its activities, in paticular the products or services offered by such enterprise;

ረ) ማናቸውም የንግድ ዕቃ በተወዳዳሪዎች እንዳይመረት ወይም እንዳይከፋፈል ወይም ማንኛውም አገልግሎት እንዳይሰጥ ለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የመግታት፣ የመከልከል ወይም የማዳከም ድርጊት፣

ሰ) ማናቸውም ዕቃ ወይም አገልግሎት ወቅታዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዳይመረት ወይም አገልግሎት እንዳይሰጥ የመግታት ወይም የመከልከል ድርጊት።

ሸ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱትን ዕቃዎች ለማጥፋት ወይም ለመጉዳት ወይም በነዚህ ዕቃዎች ላይ ያለውን ማንኛውንም የንግድ ክፍል ለመገደብ ወይም በሞኖፖል ለመያዝ በማሰብ የነዚህ ዓይነት ዕቃዎች በተሰሩበት አገር ዋና ገበያዎች ከሚሸጡበት የገበያ ወይም የጅምላ ዋጋ ባነሰ ዋጋ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት፣

ቀ) ሚኒስቴሩ ሳይፈቅድ በማንኛውም ሁኔታ ለዕርዳታ ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ ዕቃዎች መነገድ፣

## ፲፩· ገበያን በበላይነት አለአግባብ ስለመጠቀም

፩· ማንኛውም ሰው ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን የገበያ ድርሻ በበላይነት ለመቆጣጠር የሚያስችል ወይም የሌሎችን የገበያ ድርሻ ሊቀንስ የሚችል ወይም በማንኛውም ሁኔታ ነፃ ውድድርን በመገደብ በገበያ ዕድገት ላይ ጎጂ ተፅዕኖ ያደረሰ ወይም ሊያደርስ የሚችል የንግድ ሥራ መሥራት አይችልም።

፪· በተለይም የሚከተሉት ድርጊቶች ገበያን በበላይነት ያለአግባብ የመጠቀም ድርጊቶች እንደሆኑ ይቆጠራሉ፣

ሀ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተገቢ ያልሆነና እጅግ የናረ ወይም የወረደ የመሸጫ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ መጠየቅ ወይም አቅርቦትን መገደብ ወይም ሌላውን ከንግድ ሥራ ለማገድና ላለማስገባት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ መሥራት፣

ለ) በዕቃ ገዥዎች ወይም በአገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ወይም የገበያን ዕድገት የሚቀንስ ተግባር መፈጸም፣

ሐ) አንድ ዓይነት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለተጠቃሚዎች እኩል ባልሆነ ድርድር መሸጥ ወይም ክፍያ መቀበል፣

መ) አንድ ዓይነት ዕቃዎችን ለነጋዴዎች እኩል ባልሆነ ድርድር መሸጥና አንዳንዶቹን የመወዳደር ችሎታቸው በሚቀንስበት ሁኔታ ላይ መጣል፣

ሠ) አንድን ዕቃ ወይም አገልግሎት ለመሸጥ ገዥው ያልፈለገውን ሌላ ዕቃ ወይም አገልግሎት አብሮ እንዲገዛ ማስገደድ፣

ረ) ስለንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥራት፣ ብዛት፣ መጠን፣ አሠራር፣ ውሁድ፣ ጥንካሬ ወይም ዕቃዎቹ ስለሠሩበት ወይም አገልግሎት ስለሚሰጡበት ጊዜና ቦታ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታዎች ሀሰተኛ ወይም አሳሳች የንግድ መግለጫ ወይም ማስታወቂያ ማውጣት፣

ሰ) የንግድ ዕቃዎችን መደበቅ፣ ወይም በመደበኛው የንግድ መስመር ለሕዝብ እንዳይሸጡ ማድረግ ወይም መያዝ፣

ሸ) በቂ ባልሆነ ምክንያት ማናቸውንም የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለተጠቃሚዎች አልሸጥም ማለት፣

ቀ) ተገቢ ውድድር እንዳይኖር ለማድረግ የማምረቻ ወጪን በማይሸፍን ዋጋ መሸጥ።

(f) Any act that directly or indirectly restricts, impedes or weakens the competive production and distribution of any commercial good or the renderding of any service.

(g) Any act that restricts or debars the timely or economic means of producing or distributing any good or rendering of any service;

(h) The importation of any goods from any foreign country into Ethiopia at a price less than the actual market price or wholesale price of such goods in the principal markets of the country of their production with the intent to destroy or injure the production of such goods in Ethiopia or to restrict or monopolize any part of trade in such goods;

(i) Trading in any manner in goods imported into Ethiopia for humanitarian purpose, without authorization by the Ministry;

## 11. *Abuse of Dominance*

1) No person may carry on trade which gives opportunity to control a relevant market for goods or services; or limit access to a relevant market or otherwise unduly restrain competition, having or being likely to have adverse effects on market development.

2) The following practices shall in particular be deemed to be abuse of dominance.

(a) The direct or indirect unfair imposition of excessively high or low selling price or service fee or withholding supply or any preemptive behavior to impede entry in to market.

(b) Acts which may be prejudicial to buyers of goods or services or which may hamper the growth of markets;

(c) The selling of similar goods or services to consumers on unequal terms or payments;

(d) The application to dealers in transaction of unequal terms in respect of similar goods, thereby placing some at competitive disadvantage;

(e) to impose a condition of combined sales on a buyer when the goods or services so combined is not required by the buyer;

(f) Issuance of any false or misleading commercial statement or notice, concerning goods and services in respect of their quality, quantity, volume, manufacturing process, component, strength, or the time and place of the production of goods or the rendering of services, or other similar conditions;

(g) Hoarding, diverting or withholding goods from normal trade channels;

(h) Refusing sales of goods or services to customers without good cause.

(i) Selling at a price that does not cover production cost to eliminate fair competition.

## ክፍል ሦስት
## አጣሪ ኮሚሽን

**፲፪· ስለኮሚሽኑ መቋቋም**

ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ የሆነና በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ የሚያውል አጣሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል።

**፲፫· ስለአባላቱ**

፩· ኮሚሽኑ ከመንግሥት፣ ከግል ድርጅቶች እና ከተጠቃሚዎች ማኅበር የተመረጡ አባላት ይኖሩታል።

፪· የኮሚሽኑ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማሉ።

**፲፬· ስብሰባ**

፩· ኮሚሽኑ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪· በኮሚሽኑ ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፫· ኮሚሽኑ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል። ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

**፲፭· የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

፩· ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሟል ከሚል ማንኛውም ወገን የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች መመርመር፣

ለ) የምርመራ ተግባሩን ለማከናወን አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን መረጃዎችንና ሰነዶችን ማንኛውም ሰው እንዲያቀርብለት የማስገደድ፣

ሐ) ከጉዳዩ ጋር አግባብ አለው ተብሎ የሚገመተውን ማንኛውም ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ የማድረግ፣

መ) የመሐላ ሥርዓት ወይም የማረጋገጫ ቃል የመቀበልና በዚህም መሠረት ምርመራ የማድረግ፣

ሠ) በማንኛውም ድርጅት ውስጥ የኮሚሽኑን መታወቂያ በማሳየት በሥራ ሰዓት መግባትና ለምርመራ ሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን የመፈተሽ፣

ረ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሙያዎች እንዲመደቡለት ወይም እንዲቀጠሩለት ሚኒስቴሩን በመጠየቅ ሙያዊ ጥናት የማድረግ፣

ሰ) የቀረቡለትን አቤቱታዎች መርምሮ እንደአግባቡ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና/ወይም የቅጣት ውሳኔ የመስጠት።

፪· ኮሚሽኑ የወሰነው ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ በሚኒስትሩ መፅደቅ አለበት።

፫· ሚኒስትሩ ከኮሚሽኑ የቀረበለትን ማንኛውንም አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ ሊያጸድቅ፣ ሊያሻሽል ወይም እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል።

፬· ኮሚሽኑ ኃላፊነቱን በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት በሚያስችለው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ከፊል በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት እንዲከናወን መወከል ይችላል።

**፲፮· የማስፈፀም ሥልጣን**

፩· በኮሚሽኑ ተወስኖ በሚኒስትሩ የፀደቀውን አስተዳደራዊ እርምጃ እና/ወይም የቅጣት ውሳኔ የማስፈፀም ሥልጣን በዚህ አዋጅ ለሚኒስቴሩ ተሰጥቷል።

፪· ሚኒስቴሩ ማንኛውንም የአስተዳደር እርምጃ እና/ወይም የቅጣት ውሳኔ ለማስፈጸም ፖሊስን ለማዘዝ ይችላል።



## PART THREE
## *Investigation Commission*

*12. Establishment*

*It is hereby established an investigation commission which is accountable to the Minister (hereinafter referred to as the "Commission") to exercise such powers and discharge functions as are conferred on it by this Proclamation.*

*13. Composition*

1) The Commission shall have members selected from Government, private organs and consumers association.

2) Members of the Commission, including the Chairman thereof, shall be appointed by the Prime Minister upon the recommendation of the Minister.

*14. Meetings*

1) The Commission shall meet regularly once in a month. However, it may hold extraordinary meetings at any time as necessary.

2) There shall be a quorum where more than half of the members are present at meetings of the Commission.

3) Decisions of the Commission shall pass by majority vote, however, the Chairman shall have a casting vote in case of a tie.

*15 .Powers of the Commission*

1) The Commission shall have the following powers:-

(a) to investigate complaints submitted to it by any aggrieved party in violation of the provisions of this Proclamation;

(b) to compel any person to submit information and documents necessary for the carrying out of commission's duties.

(c) to compel witnesses to appear and testify at hearings;

(d) to take oaths or affirmations of persons appearing before it, and examine any such persons.

(e) to enter by Showing the commission's ID card and search the premises of any undertaking during working hours, in order to obtain information or documents necessary for its investigation.

(f) to appoint or employ, upon the approved of minister, experts to undertake professional studies as may be necessary;

(g) to take administrative measures or/and give penalty decisions on any complaints submitted to it.

2) Any administrative measures or penalty decisions made by the Commission shall be approved by the Minister.

3) The Minister may approve, amend or remand for review any decision of Administrative measure or penalty submitted to him by the commission.

4) The Commission may delegate part of its powers and duties to the Secretariat to the extent necessary to efficiently discharge its responsibilities.

*16. Power of Execution*

1) The Ministry is hereby authorized by the Proclmation to execute any administrative measures or/and penalty decisions given by the Commission and approved by the minister.

2) The Ministry may order the police in order to execute any administrative measures or/and penalty decisions.

፫· ማንኛውም የአስተዳደር እርምጃ እና/ወይም የቅጣት ውሳኔ ከመፈፀሙ በፊት ለሚኒስትሩ ቀርቦ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል በጽሑፍ መፈቀድ አለበት።

፬· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚፃፈው ደብዳቤ ግልባጩ አፈፃፀሙ ለሚመለከተው ነጋዴ መስጠት አለበት።

፲፯· ይግባኝ

፩· ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ እና/ወይም የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው እንዲፈጸም መፈቀዱን ደብዳቤ ደርሶት ካወቀበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

፪· ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተወሰነው የይግባኝ ጊዜ በፊት የማንኛውንም ውሳኔ አፈፃፀም መጀመር አይችልም።

፲፰· የጽሕፈት ቤቱ ተግባራት

፩· ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) በኮሚሽኑ የወጡትን መመሪያዎች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የአስተዳደር እና/ወይም የቅጣት ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ቃለ ጉባዔዎች፣ ሪፖርቶች፣ ውሳኔዎችና ሌሎች ሰነዶች ይይዛል፤

መ) የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በተመለከተ የሕዝቡን ንቃተ ሕሊና ለማሳደግ የሚረዱ የተለያዩ መድረኮች ያዘጋጃል።

፪· በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት የሚከናወኑ ሌሎች ዝርዝር ተግባራት በኮሚሽኑ ይወሰናሉ።

፲፱· የሥነ-ሥርዓት ደንቦችና መመሪያዎች

፩· ኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባሩን በተገቢ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችሉትን የሥነ-ሥርዓት ደንቦችና መመሪያዎች ያዘጋጃል።

፪· ደንቦቹና መመሪያዎቹ በኮሚሽኑ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምፅ መጽደቅ አለባቸው፤

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳· የዕቃዎችን ዋጋ ስለማመልከት

፩· ማንኛውም ነጋዴ እንደአስፈላጊነቱ የንግድ ዕቃዎቹንና የአገልግሎቶቹን የዋጋ ዝርዝር በንግድ ቤቱ በግልጽ ሥፍራ በሚታይ ቦታ ማመልከት ወይም በንግድ ዕቃዎቹ ላይ መለጠፍ አለበት።

፪· የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ዋጋ ቀረጥ፣ ታክስ ወይም ሌላ ሕጋዊ ክፍያ ያካተተ ይሆናል።

፳፩· ስለንግድ ዕቃዎች መግለጫ

፩· ማንኛውም ነጋዴ በሚሸጣቸው የንግድ ዕቃዎች ላይ እንደአስፈላጊነቱ መግለጫ መለጠፍ ወይም በተለየ ወረቀት ላይ ጽፎ ለገዢው መስጠት አለበት።

፪· በንግድ ዕቃዎች ላይ የሚደረግ መግለጫ እንደአግባቡ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የሚያመለክት መሆን አለበት፤

ሀ) ዕቃዎቹ የተሠሩበት ወይም የመጡበትን አገር፤

ለ) የዕቃዎቹን ክብደት፣ መጠን እና ብዛት፤

ሐ) የዕቃዎቹን ጥራት፤

መ) ዕቃዎቹ ከምን እንደተመረቱ የሚያሳይ ዝርዝር፤

ሠ) ዕቃዎቹን የቴክኒክ ዝርዝሮች፣ የአሠራር ወይም የአጠቃቀም ዘዴ፤

3) Any administrative measures or/and penalty decisions shall be executed after obtaining approval of the Minister in writing.

4) Copy of the letter to be written in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be given to the trader concerned.

17. *Appeal*

1) any party may appeal to the Federal High Court against any administrative measures or/and penalty decisions within 30 days from the date that he was aware of the approval of the execution.

2) The Ministry shall not commence the execution of any decision before the expiry of the period laid down under Sub-Article (1) of this Article,

18. *Duties of the Secretariat*

1) The Secretariat shall have the following duties;

(a) implement the directives issued by the Commission.

(b) execute administrative measures or/and penalty decision.

(c) keep minutes, reports, decision and other documents of the Commission.

(d) prepare forums and disseminate information to enhance public awareness regarding the implementation of this Proclamation.

2) Other functions to be performed by the Secretariat shall be determined by the Commission.

19. *Rules and Directives of Procedures*

1) The Commission shall develop rules and directives of procedures to efficiently undertake its powers and duties.

2) The rules and directives of procedures shall be approved by two third of members of the Commission.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS

20. *Indications of Prices of Goods*

1) Any trader shall, as necessary, display a price list for his goods and services by posting such list in a conspicuous place in his business premise or by affixing price tags on the goods.

2) Indication of prices of goods and services shall include customs, taxes and other fees.

21. *Labels of Goods*

1) Any trader shall, as necessary, fix explanatory labels on the goods for sale or provide such details to the buyer on a separate paper.

2) Labels used in connection with goods, shall as appropriate indicate the following particulars:

(a) indication of country of production or export;

(b) weight, volume and quantity of the goods;

(c) quality of the goods;

(d) statement of the materials used to produce the goods;

(e) technical specification of the goods and their operational or utilization methods;

ረ) በዕቃዎቹ አጠቃቀም ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸውን የደኅንነት ጥንቃቄዎች፣

ሰ) ነጋዴው ስለዕቃው አገልግሎት ለገዢው የሚሰጠውን ዋስትና፣

ሸ) የኅብረተሰቡን ጥቅም ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ አግባብ ካለው ሌላ መሥሪያ ቤት ጋር በመመካከር በሕዝብ ማስታወቂያ የሚያወጣቸውን ሌሎች ዝርዝሮች።

፫· በታሸገ ዕቃ ላይ የሚደረግ መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተገለጸው በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ማመልከት አለበት።

ሀ) የዕቃው የተጣራ ክብደት፣

ለ) የፋብሪካው ወይም የአሻጊው ስምና አድራሻ፣

ሐ) ዕቃው አገልግሎት መስጠት የሚያበቃበትን ጊዜ፣ እና

መ) ዕቃው የተመረተበትን ቀን።

፳፪· <u>የመሠረታዊ ንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ የመወሰን ሥልጣን</u>

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ያደረገውን ጥናት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማስ ፈቀድ ዝርዝራቸውንና ዋጋዎቻቸውን በሕዝብ ማስታወቂያ ሊያወጣ ይችላል።

፳፫· <u>ስለመሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች ሥርጭት</u>

አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከሚመለከታቸው ሌሎች መሥሪያቤቶች ጋር በመመካከር ዝርዝራቸውንና ዋጋዎ ቻቸው በሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጹት መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ስለሚሠራጩበት፣ ስለሚሸጡ በትና ከቦታ ቦታ ለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ለመወሰንና እንደአስ ፈላጊነቱም ዕቃዎቹ ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ ነጋዴውን ለማዘዝ ይችላል።

፳፬· <u>ደረሰኞችን ስለመስጠትና ስለመያዝ</u>

፩· ማንኛውም ነጋዴ ለሸጠው የንግድ ዕቃ ወይም አገል ግሎት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ነጋዴው ለሸጣቸው የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የሰጣ ቸውን የደረሰኝ ቀሪዎች ወይም ለገዛቸው የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የተቀበላቸውን ደረሰኞች ለአምስት ፭ ዓመት ላላነሰ ጊዜ መያዝ አለበት።

፳፭· <u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

ኮሚሽኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስ ፈጸም የወጡትን ደንቦች፣ የሕዝብ ማስታወቂያዎች ወይም መመሪያዎች በተላለፈ ማንኛውም ሰው ላይ ቀጥሎ የተመለከ ቱትን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ለመውሰድ ይችላል።

፩· አቤቱታ የቀረበበትን ድርጊት እንዲታገድ፣ እንዲስተ ካከል ወይም ጨርሶ እንዲቋረጥ ማድረግ፣

፪· የንግድ ፈቃዱን ማገድ ወይም መሰረዝ፣

፫· የተጎጂውን የመወዳደር አቅም በነበረበት ለመመለስ የሚያስችል ተገቢ እርምጃ መውሰድ፣

፬· የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ዕቃዎች በሆኑ ጊዜ ዕቃዎቹ እንዲያዙና እንዲሸጡ በማድረግ ከሽያጩ ከተገኘው ገቢ ላይ ለሽያጩ ሂደት የወጣው ወጪ ተቀናሽ ሆኖ ቀሪው ለባለቤቱ እንዲመለስ ማድረግ። ሆኖም ባለቤቱ ወለድ ወይም ሌሎች ክፍያዎችን መጠየቅ አይችልም።

(f) safety measures to be considered during the use of the goods;

(g) a warranty or guarantee of a product to be provided by the trader to the buyer.

(h) other details published in a public notice by the Ministry, in consultation with other appropriate institution, when deemed necessary to safeguard the public interest.

3) Labels on packed goods shall in addition to Sub-Article (2) of this Article indicate the following particuclars:-

(a) net weight of the good;

(b) name and address of the factory or packer;

(c) expiry date of the goods;

(d) production date of the goods.

22. *Power to Regulate Prices of Basic goods and Services*

The Ministry may as deemed necessary, submit to the Council of Ministers, its study on basic goods and services that should be subject to price regulation and, upon approval, publish the list and prices of same by public notice.

23. *Distribution of Basic Goods*

The appropriate Authority, in consultation with other concerned institutions, may determine the distribution, sales and movement of basic goods and services and, as may be necessary, order the trader to replenish the stock of same.

24. *Issuing and Keeping of Receipts*

1) Any trader shall have an obligation to issue receipts to the buyer in respect of the goods or services he sells.

2) A trader shall keep copies of receipts issued in respect of the goods or services he sells pursuant to Sub-Article (1) of this Article or receipts obtained in respect of the goods or services he buys, for not less than 5 (five) years.

25. *Administrative Measures*

The Commission may impose the following administrative measures, where any person violate the provisions of this Proclamation, Regulations, Public Notice or Directives issued for the implementation of same.

1) Suspend, correct or eliminate the practice in question;

2) Suspend or cancel business licence,

3) Take any appropriate measure that enable the victim's competitive position to be reinstated.

4) Seizure and selling of goods that are subject to price Regulations; provided that the proceeds less any selling expense shall be paid to the owner, who in no case shall demand interest or any other payments.

፳፮· ቅጣት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሠረት የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡትን ደንቦች የሕዝብ ማስታወቂያዎች ወይም መመሪያዎች በተላለፈ ማንኛውም ሰው ላይ ቀጥሎ የተመለከቱትን ቅጣቶች ሊወስን ይችላል።

፩· በአማራጭ የአጥፊውን ጠቅላላ ንብረት ዋጋ እስከ አስር በመቶ ወይም የአጥፊውን ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ እስከ አስራ አምስት በመቶ ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ።

፪· በተከለከለው ማናቸውም ተግባር ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የማንኛውም ግለሰብ ተባባሪነት መኖር ከተረጋገጠ ጥፋት ባደረገው ሰው ላይ ከብር ፭ሺ ብር (አምስት ሺህ ብር) እስከ ፶ሺ (ሃምሳ ሺህ ብር) ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ።

፳፯· ስለመቀጮ አወሳሰን

የመቀጮውን ልክ ለመወሰን ኮሚሽኑ የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት፣ የደረሰውን ጉዳት የአጥፊውን የገበያ ተሳትፎ፣ በድርጊቱ ጉዳት የደረሰበትን ገበያ መጠን እና የአጥፊውን የገንዘብ አቋም ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

፳፰· የሕዝብ ማስታወቂያ ስለማውጣት

አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የሕዝብ ማስታወቂያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፳፱· ደንብ የማውጣት ሥልጣን

እንደ ጉዳዩ አግባብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የክልል መስተዳድር ምክር ቤቶች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጡ ይችላሉ።

፴· የተሻሩ ሕጎች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ዓይነት ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር ተፈጻሚነት አይኖርውም።

፴፩· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

26. *Penalties*

Without prejudice to administrative measures that may be taken pursuant to Article 25 of this Proclamation, the Commission may impose the following penalities, where any person violates the provisions of this Proclamation or Regulations, Public Notice or Directives issued for the implementation of same.

1) Fine upto 10 per cent of the value of total assets of the violator or 15% of yearly gross total sales of the violator, alternatively.
2) Fine from 5,000.00 (five thousands) upto Birr 50,000.00 (fifty thousands) where the direct or indirect co-operation of any indivudual in any prohibited practice is proven.

27. *Assessment of Fine*

In fixing the amount of fine, the Commission shall take into consideration the seriousness of the offense, the damage caused, the market share of the violator, the size of the market affected, and the financial status of the violator.

28. Issuance of Public Notice

Appropriate authority may issue Public Notice necessary for the implementation of this Proclamation.

29. *Power to Issue Regulations*

The Council of Ministers or the Regional Councils may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

30. *Repealed laws*

Any law or practices inconsistent with this proclamation shall be inaplicable with regard to matters provided for in this proclamation.

31. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 17th day of April, 2003.

*Done at Addis Ababa, this 17th day of April 2003.*

*GIRMA WOLDE GIORGIS*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE